.. ተማክሮ የፈሱት ፈስ አይገማም

.. በሬና በሬ መከሩ ቀንበር ሰበሩ

1069. ቦረይ ዴእዮጌ ከርያ ጎይሽን አይሰይ ዴእዮጌ ዱልያ ትዩስ

. በሬ ያለው ደጁን ሲያርስ ቅቤ የተረፈው ቂጥ ይቀባል

.. ገንዘብ ካለ በሰማይ መንገድ አለ

.. ያለው የእንጀራ እናቱን ተገኳር ያወጣል

1070. ቦረይ ጎይን ፐረይ ሜስ

. በሬ ያረሰውን ፈረስ ይበላል

.. ብላ ባለኝ እንዳባቴ በቆመጠኝ

.. አህያ የተጫነችውን ፈረስ ይበላል

.. መታደል ነው እንጂ አይታገሉም

1071. ቦረይ ጢካ አግድ ቆጣ ላጩስ

. በሬ የቀለበውን ትቶ የቀጠቀጠውን ይልሳል

.. በሬ ካራጁ ይውላል

1072. ቦራ ቀከደይ ባስ ኩንዴስ

. በሬ የረገጠ ለራሱ ይወድቃል

.. ግድግዳውን የሚገፋ ለራሱ ይወድቃል

.. አይመጣምን ትተሽ ይመጣልን በጨመርሽ

1073. ቦራ ቀይጨነው ከጭያ ኮሻ ቢደ ሀሬ ሀይታ ጠይድ ዩስ

. በሬ ለመውጋት ቀንድ ፍለጋ የሄደው አህያ ጆሮውን አጥቶ (ተቆርጦ) ይመጣል

.. አተርፍ ባይ አጉዳይ

1074. ቦራ ካተይ ያድን ኤከነ ጊድ ቦዘ ከነይ ሶግደ ጌሌስ

. ሞኝ ውሻ የበሬ ቆለጥ ሲወድቅ አነሳለሁ ብሎ ሶግዳ (ቦታ) ይገባል

.. ቀበሮ የበሬ ቆለጥ ይወድቅልኛል ብላ ስትከተል ዋለች

1075. ቦራ ኬሴነ ገዴ ቦረ ዎሬስ

. የበሬን ዋጋ የማያወጣ መሬት በሬ ይገላል

.. አያድን ጋሻ ቂጥ ያስወጋል።

1076. ቦራ ፔሼነ ገዴ ቦረ ዎሬስ

. በሬ የማያውል ቦታ በሬ ይገድላል

.. አያድን ጋሻ ቂጥ ያስወጋል

1077. ቦር ደርን አጌ ጐዬስ

. በሬ ሲበዛ መንገድ ያርሳሉ

.. ዝሆን ቂጡን ተማምኖ ግንድ ይውጣል

1078. ቦርኩ ቦጪንኔ ሱለነ፣ አጊንኔ ሱለነ

. ቦርኩ (ውሻ) ጮኸም ይታነቃል፣ አልጮኸም ይታነቃል

.. የማይቀር እዳ የሞት እንግዳ

.. የቁርጥ ቀን

.. ምንም ብታፈገፍጊ ከግድግዳ አታልፊ

1079. ቦርያ ኤሬናረ ኔአዬ ቦታ አቻ መ ገውሱ

. ስድብ የማታውቅ የናትሽን ነጭ ጥርስ ብዬ ትላለች

.. ያላዋቂ ሳሚ ንፍጥ ይለቀልቃል

1080. ቦሸ ለይት ገወረይ አውጪዬስ

. በበሽታ ዘመን ድመት ታስወርዳለች

.. በንብ ጊዜ ዝንብ ይነክሳል

.. ነብር ባየለበት ዘመን ድመት ይኮረታል

1081. ቦሸይ ሲቅዮ አዬ ናታ ሱልአ ተመይ ሚስ

. ውርጃ የሚወዳትን ሴትዬዋ ልጆች የሽልጦ እሳት ይበላቸዋል

.. ለሰበበኛ ቂጥ መረቅ አታብዛበት

1082. ቦሸይ ዶስዮ ምሸሬ ናተ ዲሌ ሜስ

. ውርጃ የሚወዳትን ሴት ልጆች ጐርፍ ይወስዳቸዋል

.. በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ

.. በቦሃ ላይ ቆረቆር

.. ለሰበበኛ ቂጥ መረቅ አታብዛበት

.. የተከፋ ተደፋ

1083. ቦሻያ ሉሳዋ ዬለውሱ

. ሙሾ አውራጅ እስክስታ ወራጅ ትወልዳለች

.. ያልዘሩት አይበቅልም

.. የዘሬን ብተው ያንዘርዝረኝ

1084. ቦቂ ዘሬቱስ ቦሮቆይ ጠይ ኤሬነ

. ቦቃ ላም ዘር ግንባር ላይ ቦቃ አይጠፋም

.. የዘሬን ብተው ያንዘርዝረኝ

.. ያልዘሩት አይበቅልም

1085. ቦቂ ዘሬተን ቦሮቆይ ጠይኮ ጥልቂ ጠዩነ

. በቦቄ (ላም) ሽንት ቦሃነት ቢጠፋ ዝንጉርጉርነት አይታጣም

. የዘሬን ብተው ያንዘርዝረኝ

.. ያልዘሩት አይበቅልም

1086. ቦብ ቦሎቴታፕ ሻባ ሚህያ ኮተይያ ሎአ ጌስ ቦሎይ

.ከቦቢ አማችነት ሻባ ከብት የጋራ የምታረባ ትሻላለች ይላል አማች

.. ውሻ ወደበላበት ይጮሃል

1087. ቦተ ኩቴስ ሶይኔ ዎሰነ፣ ከሬኔ ዎሰነ

. ለነጭ ዶሮ እቤትም ሆነ ውጪ ጠላት አይታጣም

. ቆንጆና እሸት አይታለፍም

1088. ቦተይ ይባታ ዎጤስ

. ነጭ የእርሙን ይሮጣል

.. ሌባ እንደሚፀድቅ ይምላል

1089. ቦንጐት ሼአይኔ ዎርዶ ኦደይኔ በው ኤኪስ

. ተንጋሎ የሸናና ሀሰት የተናገረ በራሱ ላይ ይደርስበታል

.. ስራ ለሰሪው እሾህ ላጣሪው

.. ተንጋልለው ቢተፉ ተመልሶ ባፉ

1090. ቦኔ ቡኪ? ቦር ዩሊ?

. በጋ ይዘንባል? በሬ ይወልዳል?

. እሪያ በሬ አይደለም

.. የማይሆን ነገር ለሚስትህ አትንገር

1091. ቦኔ ቦጋዬ አወይ ጩግን ኡቶ ዱሌ ሰኪስ

. የቦኔ ቦጋዬ አባት ሲያረጅ የተቀመጠበት ቂጥ ያመዋል

.. ካረጁ አይበጁ

1092. ቦኔ በይ ጨርኮረ፣ በልጐበይ ድኦረ

. የበጋ ነገር ከንፋስ ጋር የክረምት ነገር ከጎርፍ ጋር

.. ሁሉም ነገር ያልፋል እስከሚያልፍ ያለፋል።

1093. ቦአን ዎደ እረይ ሲርያው አይ አሺ?

. መላጣ ላይ የወረደ ዝናብ ለአፍንጫ ምን ያህል ይቀረዋል

.. የተነቃነቀ ጥርስ ሳይወልቅ አይቀርም

.. አይንና አፍንጫ

1094. ቦአን ዎድደ እረይ ሲርያ ገከነው ኣጥን ቀመይ ኡቲ

. መላጣ ላይ የወረደ ዝናብ አፍንጫ ላይ ለመድረስ ስንት ቀን ይቀረዋል

.. አይንና አፍንጫ

1095. ቦዘ ሾሸይ ናኣ ዱኬስ

. ሞኝ እባብ ሁለቴ ይነድፋል

.. የሞኝ ለቅሶ መልሶ መልሶ

1906. ቦዘ ነአይ በ አዋ በልየን ካኤስ

. ሞኝ ልጅ ባባቱ ለቅሶ ላይ ይጫወታል

.. ሞኝ ወታደር ሚስቱን ጥሎ መንደር

1097. ቦዘ ከነይ ኤሰ ኬታ ጌሌስ

. ሞኝ ውሻ ጠጅ ቤት ይገባል

.. አህያ ወደ ሊጥ ውሻ ወደ ግጦሽ

1098. ቦዘ ጌለእያ ሚዛ ሄምየ ነኣረ ዝንአውሱ

. ሞኝ ልጃገረድ የከብት እረኛ ይተኛታል

.. የሞኝን ጠላ በለው ባንኮላ

1099. ቦዘ ጌለእያ በ እሻፔ ሻረውሱ

. ሞኝ ልጃገረድ ከወንድሟ ታረግዛለች

.. በደግነቱ ተቆረጠ አንገቱ

.. አይነ አፋር ልጃገረድ ከወንድሟ ታረግዛለች

1100. ቦዘይ በር ሚዜ አሹዋፔ አቴስ

. ሞኝ ከላሙ ቅርጫ ሳይበላ (ሳያገኝ) ይቀራል

.. ሞኝ ሰው ራቱን ለሰው ሰጥቶ ራሱ ጦሙን ያድራል

1101. ቦዘይ ቦይያ ቀዬ ሚድ ኡሉወ ተማ ቤሴስ

. ሞኝ ጥሬ ‹ቦዬ› ምግብ በልቶ ሆዱን እሳት ያሞቃል

.. ሞኝ እንደመከሩት

1102. ቦዝያ ዱርን ደቦይ ዩለቴስ

. ሞኝ ስትጨፍር የሞኝ ዘመድ ያፍራል

.. ሞኝ ባያፍር የሞኝ ዘመድ ያፍር

1103. ቦዜ ዱልያ ኩቶይ ካቪስ

. የሞኝን ቂጥ ዶሮ ይጭራል

.. የሰው ቃሪያ እስኪሞት አይበስልም

1104. ቦዜሮ ቦኔ ማነ ጭንጩሮ በልጎ ማነ

. የሞኝን በበጋ የብልጥን በክረምት እንበላለን

.. ከሞኝ ደጅ ሞፈር ይቆረጣል

.. በበጋ እሞኝ ቤት ተንጋጋ በክረምት እቤትህ ተከተት

1105. ቦዜስ ቦይነይ ቁሳ

. ለሞኝ ጐደሬ እርገሞ ነው

.. ያላየ ልጅ ዳቦ ፍሪዳው

1106. ቦዜስ ከዮይ መርከ

. ለሰነፍ ሀዘን ምስክር ነው

.. በልጅ አመካኝቶ ይበሏል አንጉቶ

.. በሰበቡ መምሬ ተሳቡ

1107. ቦይነ ሽንቁ ላጠ ላጠ ጌስ

. የጎደሬ ስንቅ ብላ ብላ ይላል

.. ትንሽ ያላት እንቅልፍ የላት

1108. ቦይነ ሽንቁ ላጠ ላጠ ጌስ ቁር ዱሬ ዮተ ዮተ ጌስ

. የጎደሬ ሰንቅ የያዘ ብላ ብላ ያሰኘዋል ትንሽ ሀብት ያለው ተናገር ያሰኘዋል

.. ትንሽ ያላት እንቅልፍ የላት

1109. ቦይን በይነ አስ ቁንጥሴነን ሚኬ ጌስ

. ጎደሬ የሌለው ሰው ላይደርቅ አልበላም ይላል

.. ጅብ እማያውቁበት አገር ሄዶ ቁርበት አንጥፉልኝ ይላል

1110. ቦይያ ሲቅያ ኡራ ነትነሬ ገኪስ

. ቦዬ (ምግብ) የሚወደውን ሰው የበሰበሰ ይደርሰዋል

.. ሲሻኝ ጢስ ወጋኝ

1111. ቦዬ መልኡዋ ደራር ኤሬስ

. የቦዬን ጣፋጭነት ደራራ ያውቃል

.. የወጥን ጣዕም ማን ያውቃል ቢሉ ቀላዋጭ

1112. ቦዬ ጩልን ቦይያ ጉጃ ጌስ

. የ‹ቦዬ› ምግብ ሲያንቀው ‹ቦዬ› ጨምርበት ይላል

.. እሾህን በሾህ

1113. ቦድ ዝንእየይ ቦታ ዲሻ፣ ጦን ቶግዮይ ሎሃ ፐራ

. ጭሮ የሚተኛ ነጭ ፍየል፣ ጦና የሚቀመጥበት የተገራ ፈረስ

.. የተማረ የተመራመረ

.. የተማረ መልካም ጥቃት አያስነካም

1114. ቦድቴ ግየይ ቦጌተነው ኢቅድ ሱጌቴስ

. የቦዲቲ ገበያ ሊዘራረፍ ሲል ይጋፋል

.. የዘፈን ዳር ዳሩ እስክስታ ነው።

1115. ቦጩዋ ሁጱየን ኦይሳ ዎትን ሱጤስ

. በቆረቆር ላይ ቅቤ ቢቀቡ ይደማል

.. ለአህያ ማር አይጥማትም

1116. ቦጩዋ ሁጵያ ዩክሽን ሚደ

. ከርዳዳ ፀጉርን እያለቀሰ ላጪው

.. ወደሽ ነው ገጣቢት

ተ

1117. ተ ምቼ ዎን ዎጋሰሽን ዎዴናይ ቶክን አገነይ ካልን ዋነ ዋነ ዎገንዱቴሽ

. እህቴ ዱሮም ወገኛ ነበርሽ አሽከር ተሸክሞ፣ ባል ተከትሎ ዱሮውንስ እንዴት ትሆኚ

.. እንኳን ዘንቦብሽ እንዲያውም ጤዛ ነሽ

1118. ተ ስንተው ጨድሽን ተ ጌዱወ ካልያጌ አይቤ? ጌስ መርፔ

. እኔ ወደፊት ስወጋ ከኋላዬ የሚከተለኝ ምንድነው? ይላል መርፌ

.. ጆሮ ለባለቤቱ ባዳ ነው

1119. ተ ነአይ ሎአባ በኤሽን ተ ኡንጨ በአይስ ገውሱ ሀርያ

. ልጂ ደህና ነገር ሲያገለል እኔ ቆጮ አገላለሁ አለ አህያ

.. ይታደሏል እንጂ አይታገሉም

.. ያልታደልሽ እንዴት አደርሽ

1120. ተ ነአይ በይረይ ላፍን ካሎይ ክይዴስ

. ታላቅ ልጂ ተበላሽቶ ታናሹ ወጣልኝ

.. እድል ፈንታ ጥዋ ተርታ

1121. ተ ነአይ እሷ ግን ሀይቆይ አጌነ

. ልጂ አንድ ነው ቢባልም ሞት አይተውም

. ያለኝ ልጅ አንድ ብቻ ነው ቢሉም ሞት አይተውም

.. የማይቀር ዕዳ የሞት እንግዳ

1122. ተ ነአይ ዱክያጌ ቀረ ጊሽን ምትያጌ ዩሌቴስ

. የሚነድፈው ልጂ ጐበዝ ነው ሲባል የሚውጥ ይወለዳል

.. እድላም አሞሌ በቅሎ ይለውጣል

1123. ተ ነአ ዩሀዋፔ ተጐዳ ደጐይ ደሮ

. ከልጂ ለቅሶ የጌታዬ ደቦ ይበልጣል

.. የበላይ አደባይ

.. የራስን ጥሎ የሰው አንጠልጥሎ

1124. ተ ኔነ ዶስኬ ግን ተከያፔ ላተሙ ቀመይ አቲስ ገውሱ

. እኔ አልወድሽም ሲላት ከተራዱ ሃያ ቀን ይቀራል ትላለች

.. የማይወዱት እንግዳ ሰባት ቀን ያድራል

1125. ተ ኔነ ግዶሮ ስያኮ ተ እምዶሮ ማከ

. ያልኩህን ብትሰማ ኖሮ የሰጠሁህን አትበላም ነበር

.. ይሉሽን በሰማሽ ገበያ ባልወጣሽ

1126. ተ አዬ በይራ በይራ ጎፐ፤ ካሉዋ ካሎ ጎፐ፣ ጦሳ ጤለ በተ

. እናቴ ታላቅ ታላቅ አትበዱ፤ ታናሽ ታናሽ አትበዱ እግዜርን አይተሽ ቁረሺ

.. ከልጅ ልጅ ቢለዩ አመትም አይቆዩ

1127. ተ ኡሎይ ጥሎ ግድን ተ ዎድረይ ሱተ ጠላለ ግዴኔ ገውሱ ጌለእያ

. ልቤ ንፁህ ሆኖ ባቴ ደም ብቻ ይሁን ትላለች ልጃገረድ

.. ባልፈሱበት ቂጥ አያፍሩበት

1128. ተ ኤርዮ ዎታ ሰአ ፕትየ ገንጅየ ጌስ ጎደሬ

. እኔ የማውቀው ሩጫ መሬት የሚጠርግ አንጀት ይላል ጅብ

.. ስንተዋወቅ አንተናነቅ

1129. ተ ኤርዮጋ ኦድየ ቀጠነይ

. እኔ የማውቀውን የምትናገር ትንሽ ሰው

.. ለቀባሪ አረዱት

1130. ተ ኤጩርያ ግዶን ቦተ ዩሌትዶገው ገወራ ነእዮ ኤከነ ጌስ

. ከአይጦች መሃል ነጭ ሆኜ ስለተወለድሁ የድመትን ልጅ ማግባት አለብኝ ይላል

.. አቅሙን አያውቅ ቶሎ አይታረቅ

.. ልቡ ተራራ

.. በቅሎ አባትህ ማነው ቢባል ፈረስ አያቴ ይላል

.. ልብ እንቅርት ለማየት ይመኛል

1131. ተ አስ ሙጥሽን ኔ አስ ጨሌተይ?

. እኔ ለማን እየመተርኩ አንተ ትታነቃለህ

.. ሲሰሩለትም አያውቅ ሲሰሩበትም አያውቅ

.. ስሱ አንድ ያንቀው አንድ ይወድቀው

1132. ተ ኬተይ ዴርያ ሾባነ ጌስ ጎደሬ

. ቤቴ ታች ጋራ ስር ነው ይላል ጅብ

.. ቁቅም ከፈስ ተቆጠረች

1133. ተ ዶግደ ዎድራ ሜንተይ ገውሱ ምሽርያ

. የረሳሁትን ጭኔን ሰበርክ አለች ሴትየዋ

.. መውለድ ሲረሳ ማሳደግ ይረሳል

1134. ተ ገዴን ከምበን ዩኬቴሽን ተነ ኩሽየን በቀ ዎረይ ገውሱ ኡዱንጥያ

. ባገሬ በከበሮ ይለቀስልኝ ነበር በጥፊ መትተህ ትገለኛለህ አለች ዝንብ

.. ካገሩ የወጣ አገሩ እስኪመለስ ቢጭኑት አህያ ቢቀመጡት ፈረስ

.. ሰው ባገሩ ሰው ነው

.. ሰው አለ ወንዙ ብዙ ነው መዘዙ

1135. ተ ጊዶሮ ስይያኮ ኔ ሞሮ ጮየነ

. ያልኩትን ብትሰማ ኖሮ የበላኸውን ታስታውክ ነበር

.. ይሉሽን በሰማሽ ገበያም ባልወጣሽ

1136. ተ ጠላላስ ጥንቆ ጊዳናፔ ዴሬራ ከሶ ጊደነ

. ለብቻዬ ስንጥር ከምሆን ከሀገር ጋር እርፍ (ገሶ) ልሁን

.. ሂድ ካገር ኑር ካገር

1137. ተ ፐጠ ዴአይደ ቦተሽን ሀይቀይቸደ ዋነ ዳመትዳነ ጌስ

. በህይወት እያለሁ ነጭ ነበርኩ ሞቼ እንዴት ጠይም ሆንኩ አለ

.. ካረጁ አይበጁ

.. እርጅና ብቻህን ና

1138. ተመ አቸ ኡቴተይ መችዮ ምቾ አቴስ

. እሳት ዳር መቀመጥ ሚስትን እህት ያደርጋል

.. አወቅሁሽ ናቅሁሽ

.. አብሮ መኖር ያናንቃል

1139. ተመኔ ላፑንቶ ኮምፕንከ ተምቦይ ሙሚ

. አስራ ሰባት ጊዜ ቢጋግሩትም ትምባሆ ድፍን ነው

.. ውሃ ቢወቅጡት እምቦጭ

1140. ተመኔ እቸሹ...ምሰ ዴሽ

. ለአስራ አምስት ጠይብ አንድ የፍየል ወርች

.. ተልባ ቢንጫጫ ባንድ ሙቀጫ

1141. ተመይ ኤቶ ሶሁዋ አግድ ገርጦ ሶሁወን ጎቤስ ጌቴስ

. እሳት በአነደዱበት ትቶ እጫሩበት ያይላል ይባላል

.. ይታደሏል እንጂ አይታገሉም

.. የበላ በለጠኝ የሮጠ አመለጠኝ

1142. ተመይ ዘማን ኣድድ ዎለይተን ኪታ ደደሄስ

. የሚደንቅ ነገር እሳት ወላይታ አገር ቤት ይከድናል

.. የቀበሮ ባህታዊ ከበግ መሃል ይዐልያል

.. ጉድ ይገርማል አህያ ከጅብ ይከርማል

1143. ተምቡወን ሸሚትደ ቶረይ ግያ ጊዱወን ጦንግን ኮንችያ ቦለን ኤቄስ

. በትምባሆ የተገዛ ጦር እገበያ መሀል ቢወረውሩት ጋያ ጫፍ ላይ ይቆማል

.. በመሸታ የተገዛ ጦር ቢወረውሩት ከድፍድፍ፣

.. ዘመድ ከዘመዱ አህያ ካመዱ

1144. ተነ አሰይ ፓጨናፔ ከልተን ተሽንጨፔ ፐሽ ኤኮ
ገውሱ ምሽርያ

. ሰው ከሚታዘበኝ በመጥረቢያ ከሸንጨ ቆርጦ ይውሰድ
ትላለች ሴትዮዋ

.. ስም ከመቃብር በላይ ይውላል

1145. ተነ እንቴ ዋት ዶሴኬት ህን ሃን ላጭሽን

. እንዴት አይወዱኝም ህ – ሃ መሸምሸም

.. ይሉኝታና ጥቅም አብሮ አይሄድም

1146. ተነደን ሜቻ ሜጨነ ጋደ ኔ ማዩዋ ሞሮፐ

. እንደኔ አጥባለሁ ብለሽ ልብስሽን አታበላሺ

.. እንቁራሪት ዝሆን አክላለሁ ብላ ፈንድታ ሞተች

1147. ተነደን ጠንተነ ጋዳ ኔ መራ ዎሮፐ

. እንደኔ አጠባለሁ ብለሽ ጥጃሽን አትግደይ

.. የፉክክር ቤት ሳይዘጋ ያድራል

1148. ተነደን ጤለነ ገይደ ኔ አይፌ ሾሎፖ

. እንደኔ አያለሁ ብለሽ አይንሽ እንዳይንሸዋረር

.. እንቁራሪት ዝሆን አክል ብላ ተሰንጥቃ ሞተች

1149. ተናረ ተመ ገውሱ ከይስያ

. ከኔ ጋር አስር ነን ትላለች ሌባ

.. ሌባን ሌባ ሲሉት ከሸንጉ ተነስቶ ይሮጣል

1150. ተናረ ተመ ጌስ ማቼ አገነይ

. ከኔ ጋር አስር ነን ይላል አቶ ባል

.. ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ

.. ስንተዋወቅ አንተናነቅ

1151. ተው ሰአይ መጨ ግዶ ሄሜተነይ ዱጌተ ግዶ

. ቀኑ የሴት ይሁን የምሄድበት ቁልቁለት ይሁን

.. መንገዱን ጨርቅ ያርግልህ

1152. ታን ኤርዮ ጎደሬ ጋሞት ጣጌስ

. የማውቀው ጅብ እንደአንበሳ ይጮሃል

.. ጅብ እማያውቁበት አገር ሄዶ ቁርበት አንጥፉልኝ ይላል

1153. ታዬ ኔ ዴአሸ ተ ዝንአ ዴንደነ ገውሱ ነእያ

. እማዬ አንቺ ቆዩ እኔ ተኝቼ ልነሳ ትላለች ልጅቷ

.. ከባልሽ ባሌ ይበልጣል ሽሮ አበድሪኝ እንዳለችው

1154. ታጋ መ ግን ሰአይ ሰንበተ ጌስ

. የኔን ብላ ቢሉት ቀኑ ሰንበት ነው ይላል

.. ሰነፍ በአል ያበዛል

1155. ታፕ አድ ብዲ አጊያን ሚቆ

. ከኔ አልፎ ሄዶ መንገድ ላይ ይሰበር

.. ከራስ በላይ ንፋስ

.. እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል

1156. ቱልያ መችዮ ቱልያ ስንተን ዎሴቴስ

. የደንቆሮን ሚስት ደንቆሮ ፊት ይለምኗታል

.. በእውር ይጠቃቀሱበታል፣ በደንቆሮ ይንሾካሾኩበታል

1157. ቱመ ያግን ቱምአ ሶሆይ ፐጢስ

. እውነት ነው ከተባለ የተወጉበት ቦታ ይድናል

.. እውነትን እግዜር ይወደዋል

.. እውነት ተናግሮ እመሸበት ማደር

1158. ቱመይ ቱጁማ ያዩነ

. እውነት ውሸትን አይፈራም

.. የእውነት በትር ትቀጥናለች እንጂ አትሰበርም

1159. ቱማ ሃሰይን ሃይቅደ ሞሌ ፐጤስ

. እውነት ከተናገሩ የሞተ አሳ ይድናል

.. እውነት ተናግሮ እመሸበት ማደር

1160. ቱማ አድን ጦሰይ ዶሴስ

. እግዚአብሔር የሚወደው ዕውነት ሲናገሩ ነው

.. እውነት ተናግሮ ከመሸበት ማደር

1161. ቱማ ዮትኬ ኑ ሹክድ ሚዶ ሞሌ ፐጤኔ ጌቴስ

. እውነት ብንናገር አርደን የበላነው አሳ አይድንም ወይ ይባላል

.. እውነት ተናግሮ እመሸበት ማደር

1162. ቱሙ ሚዘይ ዴርየን ሚሽን ከጭያረ ወከለይ ዩስ

. የዕውነቱ ከብቶች ዱር ሲግጡ እባብ ከቀንዳቸው ጋር እቤት ይመጣል

.. ለሃጥአን የመጣ ለፃድቃን ይተርፋል

1163. ቱሙ ዮሆይ መታዩ ኮሼነ

. ለእውነተኛ ነገር ጉቦ መስጠት አያስፈልግም

.. የእውነት ብትር ትቀጥናለች እንጂ አትሰበርም

1164. ቱሳስ ድጭየ ምታ ቱረይ ዛሬነ

. ለምሰሶ የታደለችውን እንጨት ሐረግ አይመልሳትም

.. ከሰው መርጦ ለሹመት ከእንጨት መርጦ ለታቦት

1165. ቱንኩልሰ ቱሰን ዎተ ግን ቱቅየን ዎቴስ

. ቱንኩልሳ ምሰሶ ላይ አስቀምጥ ሲሉት ወጋግራ ላይ ያስቀምጣል

.. ፍየል ወዲያ ቅዝምዝም ወዲህ

1166. ቱካ እጥደይ ቱንጊ ቤቴስ

. ጨርስን እምቢ ያለ ወደ አዲስ አበባ ይኮበልላል

.. ተው ቢሉት እምቢ ያለ ሩቅ መንገድ ይጓዛል

.. ምከረው እንቢ ካለ መከራ ይምከረው

1167. ቱኬ ፔንቶ ጊሽን አወይ ፔንቴስ

. ቡና ይፍላ ሲባል ፀሐይ ይፈላል

.. ጊዜ ወርቅ ነው

.. አታርፍጂው ቶሎ ጣጂው

1168. ቱገው ኤኮ መችያ ቱራደን ጣጤተውሱ

. ለችግር ያገቧት ሚስት እንደ ሀረግ ትጠመጠማለች

.. የቸገረው ዱቄት ከንፋስ ይጠጋል

.. የቸገረው እርጉዝ ያገባል

1169. ቱገይ ሀርያረ ዝንኤስ

. የቸገረው ከአህያ ጋር ይተኛል

.. የቸገረው ዱቄት ከነፋስ ይጠጋል

.. የተቸገረ እርጉዝ ያገባል

1170. ቱጁመይ ቱማ ሌእሴሽን ቱጁመይ ላሌትዮ ዎዲ ቱመይ ክይድ ዎድ ኦርዲስ

. ውሸት እውነትን ያቀላል፣ ግን ውሸት ሲጠፋ እውነት ደልቦ ይወጣል

.. እውነትና ንጋት እያደር ይጠራል

1171. ቱጁመይ ቱማ ጦኔስ

. የውሸት መበርከት እውነትን ያሸንፋል

.. ሀሰት ስለበዛ እውነት ሆነ ዋዛ

.. ውሸትና ቅራሪን ሽምጥጥ

1172. ቱሞ ተረይ አዋጅ ኤሬነ

. የነጭ ሽንኩርት ተራ አዋጅ አያውቅም

.. ያበጠው ይፈንዳ

.. ይሉኝ አይል የጓላውን አያይ

.. የጠገበ ሰው ራሱን አያስብም

1173. ቴመ ታደስ ጎሻ ቆፕዳሽን ዜሬተይ ጠዪስ ገውሱ ቃርያ

. ታደሰ ቴማ እርሻ አስቦ ነበር ዘር ጠፋ ትላለች ጦጢት

.. ሊበሉ የፈለጓትን አሞራ ይሏታል ጅግራ

.. አዛኝ ቅቤ አንጓች

1174. ቴማሞ ዎረነው ኤቂዲ ቦልአሾ ሎሾሹ አቴስ

. ቴማሜን የሚገድል ቦልአሼን ይደካክማታል

.. አቃቢት ተልባ በበላችው ገበዙን ተጋረፈው

1175. ቴረው ዬዶ ጩጎይ ቀውኢያ ኤኪ ዎዪስ

. ለጎመራው የተወረወረው ቅዝምዝም ጥሬውን ይዞ ይወርዳል

.. ለሃጥአን የመጣ ለፃድቃን ይተርፋል

1176. ቴረይ ዎቂስ፣ ፔንተይ ጉኪስ

. የጎመራ ይበሰብሳል፣ የፈላ ይገነፍላል

.. ማር ሲበዛ ይመራል

1177. ቴራ ቴጁ ሚገዚያ ዬሎ መረ ዲቺኩሽን ሀራው ቦራው ኤቀውሱ

. የቴራ ቴጁ ላም የወለደችውን ጥጃ አታሳድግም ሌላ ለመድገም ወይፈን ትፈልጋለች

. በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ

1178. ቴራስ ዬዶይ ቀውእያ ላሌስ

. ለጎመራ የተወረወረው ጥሬውን ይዞ ይወርዳል

.. ለኃጥአን የመጣ ለፃድቃን ይተርፋል

1179. ቶሆ ዶስየ ኡራ ኡንጫ ቀሾይ ገኪስ

. ሸክም የሚወድ ሰው የቆጮ እስር ይደርሰዋል (ያጋጥመዋል)

.. ተሸከም ያለው ስልቻውን ተቀመጥ ያለው ኮርቻውን

1180. ቶሆይ በር ጐዳ ኤሬስ

. ሸክም ጌታውን (ባለቤቱን) ያውቃል

.. ቁቀመጥ ያለውን ኮርቻውን ተሸከም ያለውን ስልቻውን አይነሳውም

1181. ቶሆይ በይነ ሾሸይ ገሳ ጤራ ክዩስ

. እግር የሌለው እባብ ቀረሮ ጫፍ ላይ ይወጣል

.. ጉድ ሳይሰሙ ቀኑ አይመሽም

.. የናቁት ያስረግዛል

.. አይዋጥ አይተፋ መላው የጠፋ

1182. ቶሆይ ዱሬ ዱሌ መንቆ

. እግር ሃብታም ነው ቂጥ ግን ድሃ ነው

.. መቀመጥ መቆመጥ ነው

.. ቢከፍቱት ተልባ

1183. ቶሆፔ ቶገይ ሎኦ

. በእግር ከመሄድ በከብት መሄድ ይሻላል

.. ቢያስቀዝንም ጮማ ይሻላል

1184. ቶለን ፔእደ ከነይ ቦረሳ ሜስ

. ጦሙን የዋለ ውሻ አንድ ማሳ እህል አይመልሰውም

.. የተራበ የሚጠግብ አይመስለውም

1185. ቶማ ጉተነ ጦሰይ ከጭያ ጨድሴስ

. ግዳይ ለማሳነስ የፈለገ ጌታ ቀንድ ያስወጋል

.. እድለቢስ ሲዳር ውሃ ይሞላል በህዳር

1186. ቶምፑ ኡድ ቶሬነይ ቶርቹዋ ሀፕ ኡዴስ

. በደንብ የማይወጋ መሀሉን ይነጥቃል

. በደንብ ያልቆፈረ ሰው ደህናውን ቆጮ ለመውሰድ እጁን ይሰዳል

.. በሰው ቁስል እንጨት ስደድበት

.. እንካን የማያውቅ አምጣን ማን አስተማረው?

1187. ቶረይ ሀሽየን ዴእሽን ኦለይ ዎሬስ

. ጦር እትከሻ ላይ እያለ ጦርነት ይገላል

.. የማይጠቅም ጋሻ ቂጥ ያስወጋል

.. ያህያ ባል ከጅብ አያስጥልም

1188. ቶራ መሱንት ፐጤስ፣ ዶነ መሱንት ፐጤነ

. የጦር ቁስል ይድናል፣ የአፍ ቁስል ግን አይድንም

.. በጦር የተወጉበት ቁስል ይድናል የምላስ ቁስል ግን አይድንም

.. በጦር የወጉት ይድናል በምላስ የወጉት አይድንም

1189. ቶራ ቀራ ኦል ዛርየጋ ነኣ ሶን ኡተ ዶና በለይ ከሬስ

. ተዋግቶ የሚመልሰውን ጦረኛ ልጅ እቤት ያለ አፈኛ ይንቀዋል

.. አፍ ያለው ጤፍ ይቆላል

1190. ቶራፔ አሽን ኔ ኡሸቸ ኩሽያ እመ ጌስ ማሄ

. ከአዳኝ ቢያድነው ቀኝ እጅህን አምጣ ይላል ነብር

.. ብር ላበደረ ጠጠር

.. ባጐረስኩ እጄን ተነከስኩ

1191. ቶሮርያ ግዮ ኡተይ ቶኮባ ኤክድ አዬስ

. ቶሮርያ (እንሰት) የተከሉትን ሁሉ ይዞ ይሄዳል (ይጠፋል)

.. ከአህያ ጋር የዋለች ጊደር ፈስ ተምራ ትመጣለች

1192. ቶስከዮይ ጦኔነ፣ ቶጠዮይ ጦኔስ

. ማበላሸት አያቅትም፣ ማስተካከል ያቅታል

.. መበተን አያቅትም መሰብሰብ እንጂ

.. ከመጠምጠም መማር ይቅደም

1193. ቶችዮ ከነይ ጣርዛፔኔ ግያ ሱታፔኔ አቲስ

. የሚበድሉት ውሻ ከፍርፋሪም ከገበያ ደምም ይቀራል (ይከለከላል)

.. የተከፋ ተደፋ

.. ያልታደልሽ እንዴት አደርሽ

1194. ቶከይ ዴእሽን ቶገይ ለበኔስ

. የተሸከመ እያለ በቅሎ ላይ የተቀመጠ ይደክማል

.. አቃቢ ኮሶ ጠጥተው ቂሰ–ገበዙን አሻራቸው

1195. ቶከን ሹች ዴጦ ምት ዲጦ፣ ግን እ አይ ዴጦ ሰአን ዎዲቼስ፣ ሀደር ዴጦ ጌቴስ

. ከሚሸከሙት ነገር ድንጋይ ይከብዳል ወይስ እንጨት? ቢል ሁሉም መሬት ላይ ይወርዳል፣ ከሚሸከሙት ነገር አደራ ይከብዳል ይባላል

.. አደራ ጥብቅ ሰማይ ሩቅ

.. አደራን ከመብላት የወለዱትን ልጅ መብላት

1196. ቶከን ክዩስ ቦከን ሽዩስ

. በሸከም ይወጣል ተቆፍሮለት ያራል

. ተሸከመውት ያወጡታል ቆፍረው ያሳሩታል

.. ገንዘብ ካለ በሰማይ መንገድ አለ

1197. ቶኬነን ቶንቸየ ሃሽያሬ እትመይ ኔዮ ኡቶ፤ ቶከደ ቶይለትያሬ አዴ ዩለ

. ሳትተከይ ቆራርጠሽ የምትፍቂ ቡላው ላንቺ ይጠራቀ ምልሽ፣ ተከለሽ የምታውደለድይ ወንድ ውለጂ

.. ለፍቶ መና

.. ሞኝ ወታደር ሚስቱን ትቶ መንደር

1198. ቶኬነን ቶንቸይያሬ እትመይ ኡቶ

. ሳትተከዩ የምትጨፈጭፊ ቡላው ይበርክትልሽ

.. በሰው ቁስል እንጨት ስደድበት

1199. ቶጋገ ቶከይ ከሬስ

. የተሸከመ በቅሎ ላይ ያለውን ይንቃል

.. አህያ የሌለው በቅሎ ይንቃል

.. አዳኙ ሚዳቋዋን አባርሮ ሊገድላት ስለአልቻለ ስጋሽ አይጣፍጥም አለ ይባላል

1200. ቶግ ኤርያ ኣዋ ነኣ ኮርሽን ገቴስ

. የፈረሰኛን ልጅ ሲጫን ያደርሰዋል

.. ጫን ያለው ኮርቻውን ተሸከም ያለው ስልቻውን

1201. ቶግየ ዳነይ ኮርዮ ዎዴ ገኬስ

. ፈረሰኛ ፈረስ ሲጫን ይደርሳል

.. ጫን ያለው ኮርቻውን ተሸከም ያለው ስልቻውን

1202. ቶግድ ጎችዮጋኔ ኡስትድ ጉትምዮጋኔ ገቶፓ

. ፈረሰኛ እግረኛ ከመሆንና አምጭ ሲበላ የነበረ ባዶ ሲበላ አያድርስ

.. ጊዜ ነው እንጂ ቁም ነገራም የሰው ልጅነት አያኮራም

1203. ቶገጉዋ ኩምደ ሻሻ ኦኔ ሚድ ውርስደይ

. እንቅብ የሞላውን ቆሎ ማን በልቶ ጨረሰው

.. እውነት ተናግሮ እመሸበት ማደር

1204. ቶጨን አርጉቤ ሰወናፔ ተ ዬረ በሌን ተነ ጫለ አይሰይ ሰዎ

. የቶጫ ትምባሆ ከሚሸትተኝ የአገሬ የባሌ የኮመጠጠ ቅቤ ይሽተተኝ

.. የሰው ወርቅ አያደምቅ

1205. ቶጩ ቶራ ቶኬስ

. ፈርስ ጦር ይሸከማል

.. ሆድ ይሰፋል ከሁዳድ

1206. ቶፕላ ሱቆይ ቶካሳ

. የአመዳም ፈስ ቶካሰ ነው

.. ባለጌ አፉን እንጂ እግሩን አያድጠውም

ነ

1207. ነምሰይ ኦይቅደ በይረይ ካሉዋ ኩሽያ ዩርድ ፐርሱዋ ኡዩስ

. የራበው ታላቅ የታናሹን እጅ ስሞ ጠላ ይጠጣል

.. የተቸገረ እርጉዝ ያገባል

.. ቀን እስኪያልፍ ያባቴ ባሪያ ያግባኝ

1208. ነምሰይ ኦይቅደ በይረይ ካሉዋስ ኩሼ ዩሬስ

. ረሃብ የያዘው ታላቅ የታናሹን እጅ ይስማል

.. ችግር ብልሃትን ትፈጥራለች

.. የቸገረው ዱቄት ከንፋስ ይጠጋል

1209. ነምሳፔ ከሎይ ሎኦ ሀርግያፔ ፐጠይ ሎኦ

. ከመራብ መጥገብ ከህመም ደህንነት ይሻላል

.. ቢያስቀዝንም ጮማ ይሻላል

1210. ነሽ አቅን ቡክ ዎንቴስ

. አመስግነው ቢያድሩ ዘንቦ ይነጋል

.. አስቀድሞ ማመስገን ኋላ ለሀሜት ያስቸግራል

1211. ነሽዶ ነኣ መችያ ቦሉዋ ስንታን ከሎ ዱረውሱ

. ያሞገሷት ምራት አማቿ ፊት ራቁቷን ትጨፍራለች

.. አወቅሽ አወቅሽ ቢሏት የቄስ ሚስት መጽሐፍ አጠበች

1212. ነሽዶ ነኣ መችያ ከሎ ዱረውሱ

. ያሞገሷት ምራት ራቁቷን ትጨፍራለች

.. አወቅሽ አወቅሽ ቢሏት የቄስ ሚስት መጽሐፍ አጠበች

1213. ነሽዶ ፐርሶይ ድምቦ ከጤስ

. ያመሰገኑት ጠላ (ቦርዴ) ቅራሪ ይወጣል

.. እንዴት ያገሳ ይሆን ያሉት ጥጃ ሊጠባ ይገባል

1214. ነአ መችያ ቀረ ግን ሙነቃ ቶሁወን ሙነቀውሱ

. የልጅ ሚስት ጐበዝ ነች ስትባል ቡሃቃ በእግር ትረግጣለች

.. አወቅሽ ቢሏት የቁስ ሚስት መጽሐፍ አጠበች

1215. ነአ መችያ በይሬ እ ቦሎትያ በይሬ

. ምራት ናት ታላቅ ወይስ አማት

.. ፍርድ ለተቀማጭ ወጥ ለቀላዋጭ

1216. ነአ መችያ ቦሎትዮ ምኪኩዋ ቤሰውሱ

. ምራት አማቷን ማንቋለጥ ታሳያለች

.. ከኋላ የመጣ ዓይን አወጣ

1217. ነአ መችያ ቦሎትዮ ምኪኩዋ ኤርሰውሱ

. ምራት አማቷን ማንቋለጥ ታስተምራለች

.. ልጅ ለናቷ ምጥ አስተማረች

1218. ነአ መችያ ቦሎትዮ ሜሬተይ ሄጋደን ግዴነ ገውሱ

. ምራት አማቷን አፈጣጠሩ እንዲህ አይደለም ትላለች

.. ልጅ ለናቷ ምጥ አስተማረች

1219. ነአ መችያ ቦሎትዮ ዩል ቤኤርኪት ገውሱ

. የልጅ ሚስት አማቷን ወልደው ባዩ ትላለች

.. ልጅ ለናቷ ምጥ አስተማረች

1220. ነአ ጊሽን ናአንቴስ

. ልጅ ነው ሲባል ይደግማል

.. ከልጅ አትጫወት ይወጋሃል በንጨት

.. የናቁት ያስረግዛል

1221. ነአረ ለጌቴት ሜለ ሽየን ጨድሴስ

. ከልጅ ጋር ጓደኛ መሆን በደረቅ አር ያስመታል

.. ለልጅ ጥርስን ለዝንብ ቁስልን

1222. ነአይ በይራ፤ በደለይ ሻቻ

. ልጁ ታላቅ በቆሎው የከረመ

.. ልጅ ማለት ታላቅ በቆሎ ማለት የበልግ

1223. ነአይ ዎጤስፔአትን ከሴ ኤኬነ

. ልጅ ቢሮጥም ቀድሞ አይቆርስም

.. ልጅ ይሮጣል እንጂ አይቀድምም

1224. ነአይ ፐራ ቶጌስ አዋይ ደራ ምጤስ

. ልጅ በፈረስ ይሄዳል አባት ከጥሻ ውስጥ ጭራሮ ይለቅማል

.. ይታደሏል እንጂ አይታገሉም

1225. ነአይኔ ጠምአይኔ አዲስ

. ልጅና ብትር ይቀድማል

.. ምርጥ ምርጡን ለህፃናት

.. ማር ሸጦ ምን ይገዟል ልጅ ጠልቶ ምን ይወዷል

1226. ነአፔ ነገረይ ክዩስ፤ ነገራ መተይ ቆሩወን ኤሴስ

. ጡር ወደ ልጅ ይተላለፋል፤ ግፍ ያለበት ንብ ማር ገደል አፋፍ ላይ ይሰራል

.. ያባት ዕዳ ለልጅ ያፍንጫ እድፍ ለእጅ

1227. ነአ መ ጌነ፤ ኦል ዎጠ ጌነ

. ልጅ ብላ አይልም፤ ጦርነት ሩጥ አይልም

.. ልጅ ቢያስብ ምሳውን

.. ልጅና ሴት ጨካኝ ናቸው

1228. ነአ ከትን ከሆ ግዴነ

. ልጅ ያበሰለው ለእራት አይበቃም

.. ልጅ ያቦካው ለራት አይበቃም

1229. ነአ ዮሆ ኤሄስ፤ ከን ሚቄተ ኤሄስ

. ልጅ ነገር ያመጣል ውሻ አጥንት ያመጣል

.. ከአይጥ ቤት ብቅል፤ ከውሻ ቤት ጠፍር አይጠፋም

1230. ነእ ዬሌትቤነን ከሴትድ ዬሌሎ ሸሜስ

. ልጅ ሳይወለድ አስቀድሞ ዛጐል (መጫወቻ) ይገዛል

.. ከፈረሱ ጋሪው ቀደመ

.. ወጡ ሳይወጠወጥ ወስከምቢያው ቂጢጥ

1231. ነእያ ቆልዮ ዎዴ ዬከደ አትዮ ዎዴ ሚጨውሱ

. ልጅቱ ገበታ ሲዘጋጅ ታለቅሳለች ሲቀርብ ትስቃለች

.. የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል

1232. ነእያ ተ አይ ግን ተበይ ሞሬትዴ ገውሱ

. ልጅቱ ምን ሆኜ ነው ብልቴ የተበላሸው ትላለች

. እድል ነው ወይ በደል

1233. ነእያ አንቱኩሽን ብታኔ ግታ ብርሼስ

. ልጅቱ ሳትስማማ (እሽ ስትል) ሰውዬው ሱሪውን ያወልቃል

.. ወጡ ሳይወጠወጥ ወስከምቢያው ቂጥ

1234. ነእያ አይዮ ብተይደ አርሰን ክየደ ዝንአውሱ

. ልጅ እናቷን ስታሚርት አልጋዋ ላይ ወጥታ ትተኛለች

.. ምቀኛ ከቤት ይወጣል

1235. ነእያ አይዮ ይክመ ዞሬ ጊዳ

. ልጅ እናቷን አጥብቃ ትመክራለች ይባላል

.. ልጅ ለናቷ ምጥ አስተማረች

1236. ነእያ ዶሱኩሽን ነአይ ሱሬ ብርሼስ

. ልጅቱ ሳትፈቅድ ልጁ ሱሪ ይፈታል

.. ወጡ ሳይወጠወጥ ወስከምቢያው ቂጥ

1237. ነእያ ጉፋ መልኤተይስ ጋደ በላ ቦለን ከቄተውሱ

. ልጅቱ ጭፈራ አሳመርኩ ብላ ባላ ላይ ትሰቀላለች

.. በቅሎ ሽንት አጠራ ብላ ሀፍረቷን ታሳያለች

1238. ነእዮ ዞረይዳ ኣይያ በው ሻረውሱ

. ልጂን እየመከረች እናት ለራሷ ታረግዛለች

.. ኣንቃ ለራሱ ኣይበቃ ለሰው ጠበቃ

.. ዝንዥሮ የራሷን ሳታይ በልጂ መላጣ ትስቃለች

1239. ናቅደ ነኣ ነእይ ናቴስ

. ኣባቱን የጨቆነውን ልጁ ይጨቁነዋል

.. ስራ ለሰሪው እሾህ ላጣሪው

1240. ናቱ ደቦቲተይ ኣቡ ዱልየን ጥንቆ ኤሴስ

. የልጅ ጓደኝነት ኣባት ቂጥ ላይ ስንጥር ያሰካል (ያስከትታል)

.. ከልጅ ኣትጫወት ይወጋሃል በንጨት

1241. ናቱረ ምዮ ጢሌ ዶና ኣይቴስ

. ከልጅ ጋር የሚበሉት ዱቄት ኣፍ ላይ ይቀባል

.. ከልጅ ኣትጫወት ይወጋሃል በእንጨት

1242. ናቱረ ሶይዝደይኔ ዲሻረ ቤትደይ እስኖ

. ከልጅ ጋር ትዳር የመሰረተና ከፍየል ጋር የተሰደደ ኣንድ ነው

.. ልጅ ያቦካው ለራት ኣይበቃም

1243. ናቱረ ሻሻ ግናፕ ከናረ ሼንዲራ ማነ ጌስ

. ከልጆች ጋር ቆሎ ከመብላት ከውሻ ጋር ገንፎ እበላለሁ ይላል

.. የልጅ ብልጥ እየቀደመ ይውጥ

1244. ናቱረ ቱሽከዮ በምበረ ቴስያ ኣይቴስ

. ከልጆች ጋር የሚያጠቅሱት በርበሬ ክንድ ላይ ይለጠፋል (እጅ ያበላሻል)

.. ለልጅ ከሳቁለት ለውሻ ከሮጡለት

1245. ናቱዮ ኣወይ ሁጲያ ፕቴስ ኣይያ ኡሉዋ ፕተውሱ

. ለልጆች ኣባት ራሳቸውን ያሻሻል፤ እናት ሆዳቸውን ታሻሻለች

.. እናት ለልጇ ነቢይ ናት

.. ጐሽ ለልጇ ስትል ተወጋች

1246. ናት ናአ ዶኖይ ባተ

. ልጆች ሁለት ድንች እንስራ ሙሉ

.. ሞኝ የዕለቱን ብልጥ ያመቱን

.. አቅሙን አያውቅ

1247. ናት ኩንድን ኣይያ ደገምዮጋ ኪና ኣይያ ሀይቅን ናት ደጋሞኮነ

. ልጆች ሲወድቁ እናት የምትደነግጠውን ያህል እናት ስትሞት ልጆች አይደነግጡም

.. የበሉበትን ወጪት ሰባሪ

.. የወላጅ ሆድ ቀጥቀጥ የልጅ ሆድ ቀጥ

1248. ናቺናቼ ጐንዳ ለይታፕ ለይተይ ዱመ

. ካመት አመት ልዩ ነው

.. ዘመንን ዘመን ይሽረዋል

1249. ናአይከ ሎኦሶነሽን ለበ ሚሸ ኤክክና ገውሱ ምሽርያ

. ሁለቱም ቆንጆ ናቸው፤ አታልዩ ገንዘብ ላግኝ ትላለች ሴትየዋ

.. የትም ፍጪው ዱቄቱን አምጪው

.. ሙያ በልብ

1250. ናኡ ላፋፕ እስ ምኖይ ኪሀ

. ከሁለት ሰነፍ አንድ ብርቱ ይሻላል

.. ተልባ ቢንጫጫ ባንድ ሙቀጫ

1251. ናኡ መቼ ጎደይ ሀመሳ ሃመ ጌስ

. ሁለት ሚስት ያለው ሰው የታመሰ ቆሎ አምጪ ይላል

.. ያልታደልሽ እንዴት አደርሽ

. አተርፍ ባይ አጉዳይ

.. ከሁለት ያጣ ጐመን

1252. ናኡ መቼ ጎደይ ጐሜ ጌቴስ

. ባለ ሁለት ሚስት ጩቦኛ ነው ይባላል

.. የሁለት ሴቶች ባል ይሞታል በመሀል ይባላል

1253. ናኡ ሱቁዋ ኢተይ እስፔ ዝንኦሶነ

. ሁለት ፈሳሞች በአንድነት ይተኛሉ

.. ግም ለግም አብረሀ አገግም

.. ለአፈ ግም አፍንጫ ድፍን ያገለታል

1254. ናኡ ቆቄ ሱሌት ሱሌት ካኦሶነ

. ሁለት እውሮች እየተናነቁ ይጫወታሉ

.. እውር ለእውር ተያይዞ ገደል

1255. ናኡ ብረድየን ዩስዶ ማተይ ተሙ ብረድየን ሱግን ፑዴ ጌሌነ

. በሁለት ጣት ያለቡት ወተት በአስር ጣት ተመልሶ አይገባም

.. ከአፍ ከወጣ አፋፍ

.. የፈሰሰ ውሃ አይታፈስም

1256. ናኡ ብረድያረ ክይደብ እቸሹ ብረድየን ጌሌነ ጌስ

. በሁለት ጣት የወጣ በአምስት ጣት አይገባም ይባላል

.. ቁጭ ብሎ የሰቀሉት ቆመው ለማውረድ ያስቸግራል

1257. ናኡ ቶሁዋ ጎደይ ቶጌነን ቢኬ ጌስ

. ሁለት እግር ያለው ከብት ካልተጫነ አልሄድም ይላል

.. የደላው ሙቅ ያኝካል

1258. ናኡ አይፍያ ቆቄ አጌ መተ ጌስ

. ሁለት አይኑን የታወረ መንገዱ ቅርብ ነው ይላል

.. ለተቀማጭ ሰማይ ቅርብ ነው

1259. ናኡ ኡረይ አይቅን ዎጥያጌ ዩድን ኤቅ አጌስ

. በሁለት ገላጋይ እምቢ ያለው ሲለቁት ቀጥ ብሎ ይቆማል

.. ሞኝ አያውቁብኝም ባይ

.. ሰው መሳይ በሸንጐ

1260. ናኡ ከና ዋጥን ሼንዬራኮ ደፈስ

. ሁለት ውሾች ቢጠመዱ ወደ ገንፎ ይሰባሉ

.. ዶሮ ብታልም ጥሬዋን

.. በመሸታ የተገዛ ወር ቢወረዉሩት ድፍድፍ ላይ ይቆማል

1261. ናኡ ኮታ ጎይያጌት አከትየን (ኮቃን) ዋሬትድ ሀይቆሶነ

. ሁለት የእኩል አራሾች በመውቀጫ ተደባድበው ይሞታሉ

.. አንተም ሌባ እኔም ሌባ ምን አጣላን በሰው ገለባ

.. ይብራና ይብራ ተጣሉ በሰው ሽምብራ (ወፍ፣ የውሃ ዶሮ)

1262. ናኡ ዬዶት ዎጨን ኦግያ ድጎሶነ

. ሁለት ዱዳዎች በመንጫጫት መንግድ ይከለክላሉ

.. ከእጅ አይሻል ዶማ

1263. ናኡ ጨተይ ተ ደሮ ግን ሄዙ ጨተይ ቀች ኤክ ቤስ

. ሁለት መቶ እኔ እበልጣለሁ ሲል ሶስት መቶ አስሮ ይወስዳል

.. ከአንድ ብርቱ ሁለት መድሃኒቱ

1264 ናኦ ሻሬቾይ ሰአይ እጥን ሰንታ ሚስ

. የናኦ (ቦታ) ጠንቋይ አልሆንለት ሲለው ጐመን ይበላል

.. የተቸገረ እርጉዝ ያገባል

1265. ናጨይ ነገራ ካሌቱስ

. ቀልድ ነገር ያስከትላል

.. ቀልድና ቅዘን ቤት ያበላሻል

1266. ኑሶ ውርስደይ ጉዱ ጨሎ

. ቤታችንን የፈጀው ወደ ኋላ መመልከቱ ነው

.. ይሉኝታ የራስ አሊን ቤት የፈታ

.. ያልጠረጠረ ተመነጠረ

1267. ኑሶ ጌለይ ኑነ ውርሴስ ጌስ ምኑይ

. የኛ ቤት ጠማማነት እኛን ይጨርሳል አለ እንጨት

.. ደባ ራሱን ስለት ድጉሱን

.. ስራ ለሰሪው እሾህ ላጣሪው

.. ጠላት ይወጣል ከቤት

1268. ኑሶ ፐራ ጊሽን በልየን አንጊስ

. ፈረሱ የኛ ነው ሲባል ለቅሶ ደጅ ይጥላል

.. ያመኑት ፈረስ በደንደስ

.. ያሳደግኋት ጥጃ አለችኝ በርግጫ

1269. ኔ ሀይቆይ ቱመ ግድን ኔ ነአ ድሾይ ቲነ መትኤሬኔ ገውሱ ደውትያ

. ሞትሽ እውነት በሆነና ልጅሽን ማሳደጉ እኔን ይቸግረኝ ትላለች ጣውንት

.. ማግባትሽ እውነት በሆነና ወይፈኔን በሸጥኩ

1270. ኔ ለጌቴተይ አዋ ሱሳ ግዶ

. ጓደኝነትህ እንደ ፀሐይ ወፍቾ ይቆራረጥ

.. አቅሙን አያውቅ

.. ሰው ጨፉ

1271. ኔ መላ ድርብያ ኡር ኡርቃፔ ጉፕድ ጉሱወን ኤቁስ

. እንዳንተ ያለ ችኩል ከሞቃ ላይ ዘልሎ ቅዘን ላይ ይቆማል

.. የችኩል እግር ከዘንዶ ጉድጓድ ይገባል

.. የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል

1272. ኔ መቼ መቁዋ ስየደ ተ ጤሳን ዩገ ገውሱ ኤጩርያ

. የሚስትህን ምክር ስማና ወገቤ ላይ በለኝ ትላለች አይጥ

.. ሞኝ እንደመከሩት

1273. ኔ ሞርኬ ለግያ ኡሸቸ ኩሽየን በርሰይ? ኔ ሲቆ መችዮ ሀድርሰ ኩሽየን በርሰይ?

. ጠላት ጓደኛህን በቀኝ እጅህ ታጐርሰዋለህ ወይ? የምት ወዳት ሚስትህን በግራ እጅህ ታጐርሳታለህ ወይ?

.. ጠላት ቢያባብሉት ወዳጅ ይሆናል ወይ

1274. ኔ ሹክዮይ ሹቁልያ ተ ከትዮይ ብረድያ ኔ ሼቂያዌ ምዘቅያ

. የምታርደው ሽሆና እኔ የማበስለው ጣት የምትረግመው በዘር ውቃቢ

.. እንካን የማያውቅ አምጣን ማን አስተማረው

1275. ኔ ሽጃፔ ተ መንጀቴተይ ሎኦ ገውሱ

. ካንቺ እንከን ከሞላበት ንፅህና የኔ የለየለት መንጃነት ይሻላል ትላለች

.. ከአጉል ጌትነት የጠራ ድህነት ይሻላል

.. ስንተዋወቅ አንተናነቅ

1276. ኔ ቆልኡይ ቆቄሽን ኔ ሁጵየው ቆጵየ ገይ

. ጓዳህ እውር ሆኖ ለራስህ ባርኔጣ ትፈልጋለህ

.. የምትለብሰው የላት የምትከናነበው አማራት

1277. ኔ ነኡ ቤአደ ተ ነኡ ዩረ ኤከ ያጌቴስ

. ልጅህን አይተህ ልጂን ሳም ይባላል

. ነግ በኔ

.. ወዳጅህ ሲታማ ለኔ ብለህ ስማ

1278. ኔ አወይኔ ኔ ኣይያ አይ መሌ ግን ሀኒረ ዩሽን ቤአ ጌስ

. እናትና አባትህ እንዴት ናቸው ቢሉት በዚች ሲመጡ እይ አለ

.. አይተህ ፍረድ

.. አይን ያያል ልብ ይፈርዳል

1279. ኔ አይያከ ኔነደን በሼ ጋደ ሻቴ ሸመውሱ

. እናትሽም እንዳንችው ምጣድ ነው ብላ ወጪት ትገዛለች

.. ያላወቁ አለቁ

.. ሞኝ የናቱን ተገኳር እንደ ሰርግ ይበላል

1280. ኔ አይዮ በይገን፣ ተ አይያ ኑስ ጋጩ

. እናትህን እንሽጥና የኔ እናት ለኛ ትፍጭ

.. የራሷ ጊዜ አለቀሰች የሰው ጊዜ ሳቀች

.. ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ

.. የሰውን ባህያ የራስን በጉያ

1281. ኔ አዬ ምኖቴተይ ተ አዬ ደውተቴታ ድጌነ

. የናትህ ጥንካሬ የናቱን ጣውንትነት አያስቀርም

.. ከንቱ ድካም

.. የአህያ ባል ከጅብ አያስቀርም

1282. ኔ ኦደይደ ፔእዶባ ተ እስ ሱሰን ቱከነ ጌስ

. አንተ ስታወራ የዋልከውን እኔ በአንድ ወፎች አስራለሁ ይላል

.. ነገር ቢበዛ በአህያ አይጫንም

1283. ኔ ኦዶ ኡባ ተ ኡተደ ፓጨይስ

. የምታወራውን ሁሉ ቁጭ ብዬ እታዘባለሁ

.. ሞኝ አያውቁብኝም ባይ

1284. ኔ ውቀነ ያዲ ግን ኔ ጉጀነ ያዲ? ጌስ

. ልትሰርቅ መጣህ ቢለው አንተ ልትጨምር ነው የመጣኸው ይላል

.. ብልጥ ለብልጥ አይን ፍጥጥ

1285. ኔ ዩሎ ቢት አቄ ግን በ አዋ ሱንታ ዮቴስ

. ትውልድ አገርህ የት ነው ቢባል ያባቱን ስም ይናገራል

.. ፍየሏ ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ

.. በቅሎ አባትህ ማነው ቢባል ፈረስ አጐቴ ነው አለ ይባላል

1286. ኔ ዬዴትን፣ ተ ዎጥን፣ ሄ ደጉዋ ቢድ ኡየን

. አንተ አባረኸኝ እኔ እየሮጥኩ ያንን ደቦ ሄደን እንጠጣ ይላል

.. አንተ ግፋኝ ከላይ እኔ እወድቃለሁ ከስጋ ላይ

1287. ኔነ ሾድድ ተነ ቶኮ

. አንተን ነቅሎ እኔን በቦታህ ይተክኝ

.. እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል

.. ከራስ በላይ ነፋስ

1288. ኔነ ቆጣጌ ተነ ፖሼስ

. አንተን የቀጠቀጠህ እኔን ይሞርደኛል

.. ላንተ የበነበ ለኔም ያካፋልኛል

.. ያለብሽ አለብኝ

1289. ኔነ ተ ዎንትን ቤአነ ጌስ ብተኔ

. ቆይ ነገ አይሃለሁ ይላል ሰውዬው

.. አይነጋ መስሏት ቋት ላይ አራች እንዲሉ

.. ላያውቁሽ ታጠኝ

1290. ኔኒ ጤለደ አጌነ ፕለ፣ ታኒ መይደ በርሴነ ኢተ

. አንተ ማየቱን የማትተው ተንኮለኛ እኔ ስበላ የማላጐርስ ክፉ

.. ብልጥ ለብልጥ አይን ብልጥጥ

1291. ኔው አድዮብኔ ዛለን ሼእዮጌኔ እሱዋ

. ላንተ መንገርና አለት ላይ መሽናት አንድ ነው

.. የሰው ቃሪያ እስኪሞት ድረስ አይበስልም

1292. አ መላ ሸንከን ዎረከነይ ሀይቁስ

. በርሱ አይነት ደካማ ሰው አገማችነት ቀበሮ ይሞታል

.. የማትረባ ፍየል ዘጠኝ ትወልዳለች

1293. አሀይኔ እመተይኔ አይሶ ሶሁወን አቁስ

. ሬሳና እንግዳ ባሳደሩበት ያድራል

.. ልጅና ለማኝ የሰጡትን ይቀበላል

1294. አሃ ሶ አለተይ አሞትሸን ከሬ አለተው ኤፌቴስ

. ሬሳን የቤት ምስጥ ሲመኘው ለደጁ ይወስዷል

.. አትሩጥ አንጋጥ

.. አንቃ ለራሱ አይበቃ ለሰው ጠበቃ

1295. አህኔ ሽይኔ ዎድዮ ሶሁዋ አስ ኤሬነ

. ሬሳና አር የሚወድቅበትን ሰው አያውቅም

.. እንግዳና ሞት በድንገት

1296. አለሎ ቁቃሎይ ሱምአና ሳከሎ በካለ ሙላልያ ለጥሴስ

. የመሞላቀቅ ብዛት የሱምኤን ልጅ ሰከሎ በካሎን ለጋ ዱባ ምሳ እንዲበላ ያደርጋዋል

.. ቢከፍቱት ተልባ

1297. አለንገይ በይናኮ...ከዎ

. አለንጋ ባይኖር ኖሮ አሽከር ንጉስ ነበር

.. የሰው ግብሩ አይለየው እስከ መቃብሩ

1298. አለይ ሾቤነ፣ አንስ ሾቤስ

. ብዙ እንሰት ያለው አይጋብዝም፣ ሰብእና ያለው ይጋብዛል እንጂ

.. ከብዙ ጸሎት የልብ ቅንነት

1299. አለይ ኦርድን አላ ግዶን ቦክ ምየ ኩቶይ ቦቦርጩስ

. እንሰት ሲ.ወፍር እዚያ ውስጥ ጭሮ የሚበላ ዶሮ ቦርጭ ያወጣል

.. ካለው ተወለድ ወይም ካለው ተጠጋ

1300. አለይ ውረነበይኔ አገዘነይ ሀይቀነበይ ኤሬቴነ

. ብዙ እንሰት የሚያልቅበትና ባል የሚሞትበት ጊዜ አይታወቅም

. አይመጣምን ትተሽ ይመጣልን በጨመርሽ

1301. አለገይኔ ፔቴለይኔ ጩሌነን አጌነ

. ባዕድና የቅይጥ ቂጣ ሳያንቅ አይቀርም

.. ከባዕድ ጋር የበሉት በሶ ይወጣል ደም ገርሶ

1302. አለጋ አይፍየን ሜሬሰይ ቡንቹተ

. በባዕድ አይን ቆሎ (ፈንድሻ) ከብርንዶ ይቆጠራል

.. ላላዩ ልጅ ዳቦ ፍሪዳ ነው

1303. አለጋ ዝላሰይ እሱዋ

. የባእድ የለቅሶ እንጉርጉሮ አንድ ጊዜ ነው

.. ባዕድ ስር የለውም

1304. አለጋስ ቶርጩ ፓሸ

. በባእድ አይን አንጀት እንደብርንዶ ይቆጠራል

.. ላላዩ ልጅ ዳቦ ፍሪዳው

1305. አለጋኮ ስመደ ጮመ ባጋኮ ስመደ ምተ

. ወደ ባእድ ዙረህ አኝክ ወደ ዘመድህ ዙረህ ዋጥ

.. አኝከህ አኝከህ ወደ ዘመድህ ዋጥ

.. መከራን ከዘመድ እንጀራን ከባእድ

1306. አላመይኔ አዋረይኔ (ማጣነይኔ) እሱዋ

. ቃልቻና ጌኛ አንድ ናቸው

.. ሆዱን የወደደ ማዕረጉን ይጠላል

1307. አልቃርያ ሽቱወን ከተውሱ

. የቀበጠች ወጥ በሽቶ ታበስላለች

.. አወቅሽ ቢሏት የቄስ ሚስት መጽሐፍ አጠበች

1308. አልቃሮይ ሾሎለዪስ

. መሞላቀቅ ሲበዛ እንዲሁ ያቅለሸልሻል

.. ማር ሲበዛ ይመራል

1309. አልባቶይ ፑዴታ ዎጥን እጥን ዱጌታ ዎጤስ

. አልባቶ (ስም) ዳገት ሮጦ ሲያቅተው ቁልቁለት ይሮጣል

.. የወደዱትን ሲያጡ የጠሉትን ይቀላውጡ

1310. አልቤ አ ኬታ ተመይ ሚሽን አኮጋ ቶይሰነ ቤስ

. አልቤ ቤቱን እሳት እየበላው የአኮን ቤት እሳት ለማጥፋት ይሄዳል

.. የራሷ ሲያርባት የሰው ታማስላለች

.. የራሱን ጥሎ የሰው አንጠልጥሎ

1311. አልኦ አዝና ጥንግሌ ኤፈስ

. ውድ የሆነውን ባል ጭልፊት ይወስደዋል

.. በችግር የተገኘ ነገር ሲበላሽ

.. በድህነት ላይ ስንፍና በቂጥኝ ላይ ቁምጥና

1312. አልኦ አፉታ ኡዱንጤ ላጩስ

. ተጨንቀው ያወጡትን እንባ ዝንብ ይልሰዋል

.. ከአባ ቁፍር እሸት ተበልቶለት

1313. አልኦ ጊደ፥ ኮተ ጌሌስ

. ውድ ነው ያለው ይጋራል

.. አነሰ ሲሉ ተቀነሰ

1314. አመረ ፐራደን አቴስ

. እንዳልተገራ ፈረስ ያደርገዋል

.. ባለጌ አፉን እንጂ እግሩን አያድጠውም

1315. አመኑዋ ደሮይ ሽመይንያ መንቁቲስ

. እምነት ማብዛት ሽማኔን ያደኽያል

.. እጅግም ጸሎት ለቅስፈት

1316. አመንዮ ትሬ ደውዙንተን ዎሬስ

. ያመኑት ጉበት በብስናት ይገድላል

.. ያመኑት ፈረስ በደንደስ

1317. አመንዶ መሸይ ትርየን ሜቁስ

. የተማመኑበት ቢለዋ በጉበት ይሰበራል

.. ያመኑት ፈረስ በደንደስ

1318. አመንዶይ ቀንተ አሾሽን ዎቅን አይ ኤከኔ

. የተማመኑት ሆድ ዕቃ ነበር ከበሰበሰ ምን ይወሰዳል

.. ያመኑት ፈረስ በደንደስ

1319. አመኔነ ለግያረ ኘኑወን ኘኑወን ጫቁስ

. ከማይተማመኑ ባልንጀራ ጋር በየወንዙ ይማማላሉ

.. ከማይተማመኑት ባልንጀራ ጋር በየወንዙ ይማማላሉ

1320. አማልያ ሚዝያ ማታ ደራውሱ

. አመለኛ ላም ወተት ታበዛለች (ኃይለኛ ላም ብዙ ወተት ትሰጣለች)

.. እካስ ያለ ታማሶ እጸድቅ ያለ መንኩሶ

.. ክፉ ሰው ለክፉ ቀን ይሆናል

1321. አማራ አስንችያ ማደነ ግን መይድያ ቆተውሱ

. ያማራ አሽከር ልርዳሽ ቢሏት መጂን ደበቀች

.. ልርዳሽ ቢሏት መጂን ደበቀች

1322. አሙቅያ ቶንድያ ጠንተውሱ

. እንከፍ ወፍራም ልጅ ታጠባለች

.. እድል ፈንታ ጥዋ ተርታ

1323. አምቤኔ ገምቤኔ ገሸ ጌስ ቦምቤ ቦቶሬ

. አምቤና ገምቤ እርስ በርሳቸው ይሸላለማሉ ይላል ቦቶሬ ቦምቤ

.. እሳት ካየው ምን ለየው

1324. አምንኤነ ነአ መችያ አቱመ ነአ የለውሱ

. ያልወደዱት ምራት ወንድ ልጅ ትወልዳለች

.. የፈሩት ይደርሳል የጠሉት ይወርሳል

1325. አሞይ ሀይቆ ከሬ ገቴስ

. ምኞት ከሞት ያደርሳል

.. ምኞት ያከሳል

1326. አሞይ ትየ

. ምኞት እሸት ነው

.. ሲወልዱ አይታ በጠጢን ጣለች

.. ሀ ሳይሉ ጥፈት ውል ሳይዙ ሙግት

.. ምኞት ያከሳል

1327. አሞይ አይፈፔ ሎአ

. ምኞት በአይን ከማየት ይሻላል

.. ሆዳም ሲሸከም የበላ ይምስለዋል

1328. አሞይ ዳቦ አንከይ ሶቦ

. ምኞት ዳቦ ነው፣ ብሳና ሽበታም ነው

.. ምኞት ያከሳል

1329. አራቼ ማጋሂያ አይቆሞ ጊን አራቼ ጋሰሽን አይ አይቸይ ጌስ

. የአራቼ ባዝራ ምን ዘር ነው ቢል እሱን አራቼ እያልክ ምን ትጠይቃለህ ይላል

.. ሐረጉን ቢስቡት ዛፉ ይወዛወላል

1330. አርሰ መቼ ጎደይ በኤነን ቢኬ ጌስ

. የቀይ ሴት ባል ካልታዘልኩ አልሄድም ይላል

.. የበላን ያብላላዋል

1331. አርሰ መጫሴ ጎደይ ዱቡሻ ቢኬ ጌስ

. የቀይ ሴት ባል አደባባይ (ስብሰባ) አልሄድም ይላል

.. ባለቤት የወደደው አሞሌ በሬ ይለውጣል

1332. አርሳረ ዝንእን፣ አርሰ ገርሳረ ቃጥን፣ ቆልኦን ዴእያረ አቱመ ነኣ ዬለውሱ

. የአልጋዋ ተኝታ፣ አልጋ ስር ያለችው አንቋልጣ፣ ጓዳ ያለችው ወንድ ልጅ ትወልዳለች

.. አባ ኮሶ ጠጥተው እማሆይን አሻራቸው

1333. አርሳፔ ዎዴነ አዴ ሶዶ ኤቁስ

. ከአልጋ ላይ የማይወርድ ሽማግሌ ሶዶ ገበያ ይቆማል

.. ለተቀማጭ ሰማይ ቅርቡ ነው

1334. አርስያ ከትን ካሬትያ ግሸውሱ

. ቀይዋ ያዘጋጀችውን ጥቁርዋ ታድላለች

.. የበሬን ምስጋና አህያ ወሰደው

1335. አርስዮ ሌቅየይ ከሬቴን ገይቱስ

. ቀይዋን የናቀ ጥቁር ያጋጥመዋል

.. መራጭ ይወድቃል ከምራጭ

1336. አርበፔኔ አይመሎፔኔ ግዱወን ጦሰይ ዴኤስ

. ከአርብና ከአይመሎ መሀል እግዜር አለ

.. ከመቸገር ለግዜር መንገር

.. ሰው ይጨነቃል እግዜር ያውቃል

1337. አርባቡዋ ኤከነ ምሽርያ ዲሽን ጭራጩዋ ኤከነ ገወርያ ሱሌተ ሃይቀውሱ

. ብዙ ወተት የምታገኝ ሴትዮዋ እያለች ጭራቂ የምትወስድ ድመት ታንቃ ትሞታለች

.. አንዱ ሊበላ ሌላው ያገበግባል

1338. አርባቡዋ ኤክየ ጎድያ ዬእሽን ጭራጩዋ ኤክየ ገወርያ ድርበውሱ

. ብዙ ወተት የምትወስድ ሴትየዋ እያለች ጭራቂ የምትወስድ ድመት ትቸኩላለች

. አንዱ ሊበላ አንዱ ያገበግባል

1339. አሰ መቾ ኤክደይ ሂተን ህርጌስ

. የሰው ሚስት ያገባ መኝታው ላይ ይሰጋል

.. የሰው በልቶ አያድሩም ተኝቶ

.. ሰርቆ ከማሰብ እጅን መሰብሰብ

1340. አሰ ምየ ጎሮምትዮ ከነይ ሚስ

. ሰው የምትበላዋን ቡዳ ውሻ ይበላታል

.. ለሁሉም የበላይ አለ

.. ለጌታም ጌታ አለው

.. ለትሉም አሞራ አለው

1341. አሰ ሚዛ ሾጭዮጌ ቢታ ሾኢዮጋደን ሀኔስ

. የሰው ከብት ሲመቱ መሬት እንደመምታት ነው

.. በሰው ቁስል እንጨት ስደድበት

1342. አሰ ሜንቴርሸ ቀራርዮ ዎዴ ሀራስ ደሮ መለቴስ

. የአንዱን ከንፈር ሲቀረድዱ ለሌላው ትልቅ ይመስላል

.. ለምቀኛ ቆሎ ብርንዶ ነው

.. ያንዱ ችግር ለሌላው የእንጀራ ልጁ ነው

.. የሰው ቤት ሲቃጠል ቋያ ይመስላል

1343. አሰ በርሶይ ደሬስ ዎይ ጉጤስ

. የሰው ጉርሻ ይበዛል ወይም ያንሳል

.. የሰው ከማየት የራስን መብላት

.. የሰውን ነገር ስንቱን ልናገር

1344. አሰ ቢተን ደንገርላ ዎርድ ታዋ ሀይተይ ግተ ጌስ

. በሰው አገር ገሀን ገድሎ ያባቴ ስም ትልቅ ነው ይላል

.. ጅብ እማያውቁት አገር ሄዶ ቁርበት አንጥፉልኝ ይላል

.. ስደት ለወሬ ይመቻል

1345. አሰ ቦለ ዴእየ አጮይ ተነ አሸነ ጎፐ፣ አቀ ሼሻ ሼኤነን ቁማ ሞፐ

. ሰው ላይ ያለ ዕዳ ያድነኛል አትበል፤ ያደረ ሽንት ሳትሸና ምግብ አትብላ

.. ከእጇ በጉንጩ

1346. አሰ ቦራ ጎይየ አሰው ገቶ ግን አሰ ነኣ ስንተይዳጎ አሸም ጌስ

. የሰው በሬ የምታርሱ ሰዎች ያድርሳችሁ ሲል የሰው ልጅ ያስከተሉ ጤና ይስጥልኝ ብሎ ይመልሳል

.. ብልጥ ለብልጥ አይን ፍጥጥ

1347. አሰ ነእ ኡበ ገለስከ ምገዶባ ኦዴነ

. የሰው ልጅ ምን ጊዜም ቢሆን ያበሉትን አያወራም

.. የሰው ልጅ ከማሳደግ የውሻ ልጅ ማሳደግ

1348. አሰ ነኣ ጡገነው በር ነኣ ስንተው ኣቴስ

. የሰውን ልጅ ለማቃጠል የራሱን ልጅ ያስቀድማል

.. ጅብን ሲወጉ በአህያ ይጠጉ

1349. አሰ ነአው ጊዶበይ የልዶ ነአው ፔኤስ

. ለሰው ልጅ ያሉት ለገዛ ልጅ ይሆናል

.. ስራ ለሰረው እሾህ ላጣረው

1350. አሰ ነአይ ም አድድ ፔንግየን ቁጩስ

. የሰው ልጅ በልቶ ጠጥቶ ተነስቶ ደጃፍ (በራፍ) ላይ ይጠርጋል

.. ባዕድ ስር የለውም

1351. አሰ ነአይ ዘዞቴስ፣ እድምን እቄቴስ

. ያልወለዱት ልጅ ግትር ይላል፣ ሲያቅፉት ይወራጫል (ያለቅሳል)

.. ያልወለድኩት ልጅ አባባ ቢለኝ አፌን ዳባ ዳባ አለኝ

.. የሰው ልጅ ከማሳደግ የውሻ ልጅ ማሳደግ

1352. አሰ አዋ አቦ ግን ዶን ባዴ ባዴ ጌስ

. የሰውን አባት አባባ ቢል አፍ አፈር አፈር ይላል

.. ያልወለድኩት ልጄ አባባ ቢለኝ አፌን ዳባ ዳባ አለኝ

1353. አሰ ዬተ ኤሬነይ ጦሰ ዬተ ኤረይስ ጌስ

. የሰውን ዘፈን የማያውቅ የግዜርን ዘፈን አውቃለሁ ይላል

.. ለእብለት ስር የለው ለእባብ እግር የለው

1354. አሰ ዳፍ በይነን ኮንእ ሜቄስ

. ሰው ሳይነካው ገል ይሰበራል

.. ፈሪ የሚያባርረው ሳይኖር ይሸሻል

1355. አሰ ዴሬኔ አሰረይኔ ከሎዬስ

. የሰው አገርና ሽርጥ ያጋልጣል

.. የሰው ልጅ ካለ አገሩ ጎራዴ ካለሰፈሩ

1356. አሰ ጐሴን አይፌ ፐርሱዋ ዎቶፐ

. በሰው ቅል ጠላ አታስቀምጪ

.. የተውሶ ይሄዳል ተመልሶ

1357. አሰሰይኔ አሰረይኔ ከሎዬስ

. የሰው አገርና ሽርጥ ያጋልጣል

.. ሰው ባገሩ አንበሳ በዱሩ አሳ በባህሩ

.. የሰው አገር ዝናብና የእንጀራ አባት አይምታህ

1358. አሰስ ጋዳ ዮትዮባ ኔስ ጋደ ስየ

. ለሰው ብለው የሚያወሩትን ለራስህ ብለህ ስማ

.. ወዳጅህ ሲታማ ለኔ ብለህ ስማ

1359. አሰሶ አመኖይ ደንጮረ አይሴስ

. የሰው ቤት መተማመን ከነመቀነት (በያም) ያሳድራል

.. የሰው ወርቅ አያደምቅ

.. ሰውን ማመን ቀብሮ ነው

1360. አሰባን ሚእድ በርበን ጠሌቴስ

. በሰው ነገር ተሰብሮ በራስ ገንዘብ ይጠገናል ይባላል

.. ያልታደልሽ እንዴት አደርሽ

.. የሰው ሚስት ሚስቴን ገደለች

.. አያገባው ገብቶ አያወጣው ተቀብቶ

1361. አሰባኔ አፉዋኔ ጤሊድ ከንቴቴስ

. የሰውን እቃና ገደል እያዩ ያቋርጣሉ

.. ነገርን አዳምጦ እህልን አላምጦ

.. ሰርቆ ከማሰብ እጅን መሰብሰብ

1362. አሰበው ሃበድ ግየይ ባጋፒ አቴስ

. በሰው ሃብት የሚንገበገብ ከራሱ ይቀራል

.. አሳ ጐርጓሪ ዘንዶ ያወጣል

.. የሰው ፈላጊ የራሱን ያጣል

1363. አሰበይኔ አሰረይኔ ከሎዩነን አግ ኤሬነ

. የሰው ዕቃና ትንሽ ሽርጥ ማጋለጡ አይቀርም

.. የሰው ወርቅ አያደምቅ

.. የተውሶ ይሄዳል ተመልሶ

1364. አሰባ መይ አምፓትሽን በሪባ መይ ዝንእ አቁስ

. የሰውን የበላ ሲጨነቅ የራሱን የበላ ተኝቶ ያድራል

.. የሰው በልቶ አያድሩም ተኝቶ

.. ሰርቆ ከማሰብ እጅን መሰብሰብ

1365. አሰባ ማነ ጊድ ባጋፕ አቴስ

. የሰው እበላለሁ ብሎ ከራሱ ይቀራል

.. የሰው ፈላጊ የራሱን ያጣል

1366. አሰባ አይስ መይ? ሙሰይ ሙጫ ከና ዎሬስ

. የሰውን ለምን ትበላለህ? መብላት ጅራተ ቆራጣ ውሻ ይገላል

.. የሰው በልቶ አያድሩም ተኝቶ

1367. አሰባፔ አሰራን ዎድዳጌ ደሮ

. ከሰው ነገር ነጠላ ለይ ጠብ ያለች ትሻላለች

.. የትርፍ ትንሽ የለውም

1368. አሰና አሳረ አይስየይ ሲቁዋ፣ ኮሸፔ አሸየይ ቀንእያ

. ሰውን ከሰው የሚያኖረው ፍቅር ነው፣ ከረሃብ የሚያድነው ቁርስ ነው

.. እርቅ ከወርቅ ዛላ ከምርቅ

1369. አሰና አውደሸነው...ነአ ሙሱዋረ ዩሬቴስ

. የሰውን ልጅ ለማባበል የፋቂን ልጅ ከነንፍጡ ይስሙታል

.. ጅብን ሲወጉ ባህያ ይጠጉ

1370. አሰናስ አድን ዩሎጋስ ገኪስ

. ለሰው ልጅ ያሉት ለራስ ልጅ ይደርሳል

.. ስራ ለሰሪው እሾህ ላጣሪው

1371. አሰን ደሮይ አኔ ጊን ዩሌተ ጌስ

. ከሰው ትልቅ ማነው ቢባል ትውልድ (ዘር) ነው ይላል

.. የሰው ኩራቱ በናት ባባቱ

1372. አሰው ሀሬቶፐ፣ ቢተው ሃሬተ

. ለሰው አትገዛ፣ ለመሬት ተገዛ

.. የሰው ወርቅ አያደምቅ

1373. አሰው (ዴሪያው) ሎእዳጌ በር ሁጵየው ሎኤስ

. ለሰው መልካም የሰራ ለራሱ ነው

.. ስራው ለሰሪ እሾህ ላጣሪ

1374. አሰው ጊድ ዮትዮገ ታስ ጋደ ስየ ጌቴስ

. ለሰው ብሎ ሲያወራ ለራሴ ብለህ ስማ ይባላል

.. ወዳጅህ ሲታማ ለኔ ብለህ ስማ

1375. አሰይ ሁጵያ ደድን ኤጩርያ ሀይታ ቃተውሱ

. ሰው ፀጉሩን ቢሰራ አይጢት ጆሮዋን ታነቃንቃለች

.. ሲወልዱ አይታ በጠጧን ጣለች

1376. አሰይ ሁጵያ ፕጥን ኤጩሬ ሀይታ ይጩስ

. ሰው ፀጉር ሲያበጥር አይጥ ጆሮ ይቋጥራል

.. ሲወልዱ አይታ በጠጧን ጣለች

.. ሲያደርጉ አይታ ዶሮ ታንቃ ሞተች

1377. አሰይ ምዶ ምታ መት ገከድ ቦለ ጤሌስ

. ሰው ከበላበት ዛፍ አጠገብ ሲደርስ ወደላይ ያያል

.. የለመደች ጦጣ ሁል ጊዜ ሽምጠጣ

1378. አሰይ ደቡዋኮ ሺቅን ቶጎጎይ አሻኮ ሺቁስ

. ዘመድ ከዘመዱ ሲጠጋ እንቅብ ወደ እበት ይቀርባል

.. ዘመድ ከዘመዱ አህያ ካመዱ

1379. አሰይ ዶጌታ አጌነ ብረት ሽዮተ አጌነ

. ሰው መርሳቱን ብረት ዝገቱን አይተውም

.. ከሰው ስህተት ከብረት ዝገት

1380. አሰፕ አሰይ ሎኦ፣ አሹዋፕ ፓሸይ ሎኦ

. ከሰው ሰው ይሻላል፣ ከስጋ የጭን ስጋ (ታናሽ) ይሻላል

.. ከደህና ቢደርሱ ያደርጋል እንደርሱ

1381. አሰፐ አድደጋ አንኮይ ከታፐ አድዳጋ ከፎይ ሜስ

. ከሰው የቀደመውን አሞራ ይበላል ከእህል የቀደመውን ወፍ ይበላል

.. ከጓደኞቿ የቀደመች ማሽላ ወይ ለወፍ ወይ ለወንጭፍ

1382. አሰፐ አዲዳጌ አንኩዋሰ፣ ከታፐ አዲዳጌ ከፉዋሰ

. ከሰው የቀደመ ለአሞራ ከእህል የቀደመ ለወፍ

.. ከባልንጀሮቿ ከፍ ያለች ማሽላ ወይ ለወፍ ወይ ለወንጭፍ

1383. አሰፐ ኢተይ አሰ ቦሬስ፣ አቾፐ ኢተይ ከስየን ሚጩስ

. ከሰው መጥፎ ሰውን ይሰድባል፣ ከጥርስ መጥፎ ቀድሞ ይሰቃል

.. ዝንዣሮ የቂጧን መላጣ ሳታይ በልጇ ትስቃለች

.. ሞኝ አይታወቅብኝ ባይ

1384. አሳ ማሄ በዞን ምዮ ለይት ሶን ገወረይ ሴባ ኤሴስ

. ነብር ሰውን ጫካ ውስጥ በሚበላበት ዘመን እቤት ድመት ጭገሩን ያቆማል

.. ነብር ባየለበት ዘመን ድመት ይኮርታል

1385. አሳ ቁልየው ኢጩሬ ሀይታ ቃቴስ፣ አው ሙሌ ባወሽን

. ምንም የሌለው አይጥ ሰው ሲያረግ አይቶ ጆሮውን ያነቃንቃል (ያራግፋል)

.. ሲያረጉ አይታ ዶሮ ታንቃ ሞተች

1386. አሳ ቁልየው ከነይ ግያ ጌሌስ

. የሰውን አይቶ ውሻ ገበያ ይገባል

.. ሲወልዱ አይታ በጠጧን ጣለች

.. ሳይቸግረው ውሻ ገበያ ይገባል

1387. አሳ ቁልየው ኩቶይ ፒንግያ ሆክ ጌሌስ

. የሰውን አይቶ ዶሮ በራፉን አጐንብሶ ይገባል

.. ሲሉ ሰምታ ዶሮ ገመድ ይዛ ወጣች

.. ሲወልዱ አይታ በጠጧን ጣለች

1388. አሳ አጨዋ ኤክየ ኡረይ ግተ

. የሰው ዕዳ የሚወስድ ሰው ትልቅ ነው

.. የሰውን ግፍ የሚሸከም ሰው አሸናፊ ይሆናል

.. መከራን የቻለ አሸናፊ ይሆናል

1389. አሳ ዎዘናኔ ከፎ ብረሳኔ አስ ኤሬነ

. የሰው ልብና የወፍ እርጉዝ ሰው አያውቅም

.. የወፍ ወንዱን የሰው ሆዱን የሚያውቅ የለም

1390. አሳሮ ኮይያረ ባሮ ጠየውሱ

. የሰውን የምትፈልግ የራሷን ታጣለች

.. የሰው ፈላጊ የራሱን ያጣል፣ አሳ ጎርጓሪ ዘንዶ ያወጣል።

1391. አሳዋ ዬሆይ አሌቁዋ፣ አስ በይናጋ ዬሆይ አዋ ሆኡዋ ጌቴስ

. የዘመደ ብዙ ሰው ለቅሶ ጌጥ ነው፣ ዘመድ የሌለው ሰው ለቅሶ ፀሐይ መሞቅ ነው ይባላል

.. ዘመድና ዋንጫ እያለቀሰ ይመጣል

.. ሰው በዘመድ ከብት በገመድ

1392. አስ አሰሽን አይሌደን ሸሜቴስ

. ሰው ሁሉ ሰው ነው ነገር ግን እንደባሪያ ይገዛል

.. ሰው ባገሩ ሰው ነው

.. ሰው ባገሩ፣ አንበሳ በዱሩ፣ አዞ በባሕሩ

1393. አስ ኡሎን ጨይዮ ኡር ኪስ ጨዬስ

. ሰው በሆዱ የሚሰድበው ሰው ሰውን አፍ አውጥቶ ይሰድባል

.. ለራሱ የቀለለ ሌላውንም ያቀላል

1394. አስ ኡብ ለጌ፣ ከይሶቴተፔ ዘልኤ በርጀ

. ሰው ሁሉ እኩል ነው ግን ከሌብነት ነግዶ መብላት ይሻላል

.. ከመታማት ይሻላል መስራት

1395. አስካለ ዎጥያ ከተውሱ ግን ኡተደን ዶይሰውሱ

. አስካለ ወጥ ትሰራለች ሲባል እንደ አምቾ ትቀቅላለች

.. አወቅሽ አወቅሽ ቢሏት መጽሐፍ አጠበች

1396. አስካለ ዎጥያ ከተውሱ ግን ኤቀ ቃተውሰ

. አስካለ ወጥ ትሰራለች ሲባል ቆማ ታማስላለች

.. አወቅሽ አወቅሽ ቢሏት የቄስ ሚስት መጽሐፍ አጠበች

1397. አሹዋ ሞዶ መይ ዴእሸን ተ አይስ ይምፔትየነ ጌስ

. ስጋ ጮማ የበላ እያለ እኔ ድሀው ለምን እደበደባለሁ ይላል

.. አህያውን ፈርቶ ዳውላውን

1398. አሹዋ ቃቀይ ሰንታ ሎላ ድጌስ

. የስጋ ጉጉት (አምሮት) ጐመን መጥበስን ይከለክላል

.. ምኞት ያከሳል

1399. አሹዋ ከልን ዞአ ሚዘይ ኢቴስ

. ስጋ በልቶ የጠገበ ቀይ ከብት ያስጠላዋል

.. ስጋ ያንገፈገፈው ቀይ በሬ ሲያይ ይሸሻል

1400. አሹዋ ጦመይስሽን ተው ሄ ጨምባፔ ሀመ ጌስ

. ለስጋው ያመኛ ነኝ ከመረቁ አውጪልኝ ይላል

.. ከመረቁ አውጡልኝ ከስጋው ጦመኛ ነኝ

1401. አሹዋ ፕይደ ግን ለንጥያ እስተ ጌስ

. ስጋ ቁጠር ቢሉ ጣፊያ አንድ ይላል

.. ስጋ ቁጠር ቢሉት ጣፊያ አንድ አለ

1402. አሹዋኔ አሰረ ሜቴሽን ሌሄ ኡዶቤ

. ስጋ እንኳ ከሰው ጋር ይበላል ዱባ ቁም ነገር ነወይ?

.. ብቻውን የበላ ብቻውን ይሞታል።

1403. አሽከረይ በር ጎዳ ጡመን ዴሬቁስ

. አሽከር ጌታውን በጨለማ ያፈጥበታል

.. የህልም እንጀራ

.. ያላቻ ጋብቻ ቆይ ብቻ ቆይ ብቻ

1404. አሽከረይ ቦንቼትድ በው ጎደ ግዴስ

. አሽከር ሲከበር ራሱ ጌታ ይሆናል

.. የሰው ምግባሩ ተግባሩ

.. የሰው ክብሩ ምግባሩ

.. መስራት ያስከብራል

1405. አሽከየ ስክዶ ዘዘሬ ባቄላ አቴስ

. ወሬኛ የሰፋችው ወንፊት ባቄላ ያፈሳል

.. ለወሬ የለው ፍሬ

.. አፍ ያበዛ ጥበቡ ዋዛ

1406. አሼሎይ መርከ ገውሱ አሪማ

. አሼሎ (ውቃቢ) ምስክሬ ነው፣ ትላለች አሪሜ

.. ሀሰተኛ እስከሚፀድቅ ይምላል

1407. አሼተይ አዩ ነኣፔ ሎኦ

. መቆጠብ ከናት ልጅ ይሻላል

.. ያኖሩት እንቅርት ያገለግላል

1408. አሾ ምን አግን ተ አዝና አዙ ዎዴ ገውሱ ቴረ ጎድያ

. ስጋ በልቻለሁም ቀረም በባሌ በአዙ ጊዜ አለች የቴራ እመቤት

.. ያልፈሳሁበት ዳገት የለም አለች እንሰሳ

1409. አሾ ሚነ ሾሸይ ዱክ ዎሬስ

. ስጋ የማይበላ እባብ ነድፎ ይገድላል

.. ዶሮ ላትበላው ጭራ ታፈሰው

1410. አሾይ ሰአን ዎድድ ቡረ ኤኪነን ዴንዴነ

. ስጋ መሬት ላይ ከወደቀ ቁሻሻ (ጉድፍ) ሳያነሳ አይቀርም

.. ስጋ መሬት ወድቆ አፈር ሳይይዝ አይነሳም

1411. አሾይ ይዮዎዴ ዱርሳ ጋጪውሱ አጮይ ይዮዎዴ ቤትያ ዎጠውሱ

. ስጋ ሲመጣ ዳንኪራ ትረግጣለች እዳ ሲመጣ ኮብልላ ትሄዳለች

.. የሰው በልቶ አያድሩም ተኝቶ

1412. አቀ ኬሰ አይሰ ኬሰ

. አድረህ እይ አሳድረህ እይ

.. የረጋ ወተት ቅቤ ይወጣዋል

1413. አቀ ግን እጥደይ... ሶን አቁስ

. እደር ቢሉት እንቢ ያለ ፋቂ ቤት ያድራል

.. ሲስሟት ጥላ ሲስቧት

1414. አቀነ መችያኔ አይሰነ አገኸይኔ እስ ግየን ዴእሸን ቃደይ ገቴነ

. የምትኖር ሚስትና የሚያኖር ባል አንድ ገበያ ውስጥ እየዋሉ እድል አላገጣጠማቸውም

.. ፈላጊና ተፈላጊ አይገናኙም

.. ድሃና ገበያ አይገናኙም

1415. አቀነ ቁማ በርበሬ ውርስሴስ

. የሚያድረውን ምግብ በበርበሬ አመካኝቶ ጨርሶ ይበላል

.. በሰበቡ መምሬ ተሳቡ

.. አጥፊና ጠፊ ወናፍና አናፊ

1416. አቀነ ነምሰይ አመርስ ነምሴስ

. ጦም ሊያሳድር አመሻሽ ላይ ይርባል

.. የሚውል ሆድ በጥዋት ይርባል

1417. አቅ ክዮ ጎበይ አጮ ግዴስ፣ ዋካላይ ሶ ጌልዲ ደዌ ግዴስ

. ውሎ ይደር ያሉት ነገር ዕዳ ይሆናል አባብ እቤት ገብቶ ዘንዶ ይሆናል

.. ሳይርቅ በቅርቡ ሳይደርቅ በርጥቡ

1418. አቅዮሰይ ጎንጎሎ ግን ኔ አው ኬተይ ሚሾያ ጌስ

. የሚታደርበት ዋሻ ነው ወይ ቢል ያባትህ ቤት እልፍኝ ነው ወይ ይላል

.. ላያውቁሽ ታጠኝ

.. ከሳሽ የተከሳሽን ልብ ቢያውቅ ኖሮ ከቤቱ ባልወጣ ነበር

1419. አቅዶጋ አው ኤሬስ፤ ሰሮ አቀድ ግዮገ ሾሮይ ኤሬስ

. የአዳሩን ባለቤቱ ያውቃል፣ እንደምን አደርክን ጐረቤት ያውቃል

.. ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው

.. ረሃብን ባለቤቱ ያውቀዋል ማን ይጠይቀዋል

1420. አቄነሰን ጥስኮፐ

. እማታድርበት ቦታ አታንቀላፋ

.. አያድሩበት ቤት አያመሻሹበት

.. የማያዛልቅ ጸሎት ለቅስፈት

1421. አባ ቤኤነይ ፑልቶ ገለቴስ

. አባያን ያላየ ምንጭ ያመሰግናል

.. አባይን ያላየ ምንጭ ያመሰግናል

1422. አባ ፕንቴስሽን ወዘናይ፣ አቤ ሶን አሼስ

. ልብ አባያን ሲሻገር፣ አቅም እቤት ያስቀራል

.. ሀሳብና ጉም አይጨበጥም

1423. አባመ ከይሶይ አወ ዴሬቄስ

. ጉልበታም ሌባ በባለቤቱ ላይ ያፈጣል

.. የሌባ አይነ ደረቅ መልሶ ልብ ያድርቅ

1424. አባመይ ወድን አመቴ አጨስ

. ጉልበተኛ ለደበደበው አመቱው ይክሳል

.. አይጥ በበላ ዳዋ ተመታ

.. ድሃ ተበድሎ ማሩኝ ይላል ቶሎ